# በሞርስ ኮድ ምሥጢር ፡ የተዋበቸው ኢትዮ !!!!!

ከአቤ ኮስትሬ ፡

በነቢያት ተዘክራ ! በሊቃውንት ተወድሳ !
በሚሊዮን ዓመታት የተቆጠረ ጥንታዊነቷን አድሳ
ዛሬም ብቅ ብላለች ኢትዮ ዝክረ-ታሪኳን ተንተርሳ
የድብቁ ቋት ምሥጢረ-ቋጠሮ
ጥንተ-ዘመንን ከዚህ ዘመን ጋር አነጋግሮ
ከዓለማት ፈጣሪ የታደለችውን ኢትዮ ማንም ላይደብቃት !
ታሪኳን ታሪክ አወጣላት !
እንደ ነቢዩ አሞጽ በግልጽ ተናገረላት
የምርጥ ሕዝብ ሀገር መሆኗ ተመሰከረላት !
ከርሠ-ምድርን አጥኚዎች ሲመራመሩ
የሉሲን አጽም አውጥተው የኢትዮን ቀዳማዊነት ሲያበሥሩ
ከሶስት ሚሊዮን ዓመታት ያለፈ ማንነትሽ
ዳግም በታሪክ ተዘከረ ኢትዮ ደስ ይበልሽ !
በእናት አባቱ ዕድሜ ለክቶ መቶ ዓመትሽ ነው ቢልም !
የባዕዳኑ ሮቦት ቅዠት ቢያሳብደውም
ሉሲና የሞርሱ ኮድ መጡ የኢትዮን ክብር ይዘው
አሁን ሮቦቱን ምን ይዋጠው ?
የድብቁ ምሥጢር ቋት አሁንም ይናገራል
ዛሬም ማንነትሽን ያበሥራል !
በመጪውም ትውልድ ታሪክሽ እስከ ምጽአት ይዘከራል !!

ታላቅ የጥበብ ጸጋ ከፈጣሪው የተላከለት
የፈጠረውን የሞርስ ቋንቋ ዕውን ባደረገበት ዕለት
አሪት ዘ- ኍልቀኍ ሃያ ሶስት አሥራ ሰባት 23-17
በአኒ ኤልስዎርዝ የተጠቀሰለት !
WHAT HATH GOD WROUTH ?
እግዚአብሔር የተናገረው ምንድነው ? የተባለለት !
ዓለምን ወደ ሥልጣኔ በማምጣት ስሙ የተደነቀለት
አሜሪካዊው ሳሙኤል ሞርስ ጥበብን ተመራምሮ
በራሱ ስም ሞርስ የሚሉትን የዓለም ቋንቋ ፈጥሮ
ድ- ዳ  በሚለው የሞርስ ኮድ ያንቺ ስም መደበቁን
ሳሙኤል ራሱ ሳያውቀው ውስጠ-ምሥጢሩን !
ዘራው በዓለም ላይ ጥበቡን !!
አንቺም ከጥበቡ ጋር ተዘራሽ !
ከ170 ዓመታት በላይ አስታዋሽ ባይኖርሽም
እምዬ ኢትዮ በዚያ ጥበብ ውስጥ መኖርሽን ባይነግሩኝም
ድንቅ ስምሽ በኮዱ ውስጥ ተሸምሎ !
ከጠቢባን አምልጦ ትርጉም የሌለው መስሎ !
ከሞርሱ ምሥጢር ቋት ውስጥ ዳበስሁሽ !
ጥበበኛ ነን ባዮች ሳያዩሽ አየሁሽ !
እንደ አርኪዎሎጂስቶች የከርሠ-ምድር ቁፈራ
እኔም የሞርስን ጥበብ ሳውጠነጥን ሳጣራ
በኮዱ ውስጥ ሽምልል ብለሽ ተውበሽ !!
ማንኛውም ምድራዊ ሀገር ያልተሰጠውን ክብር ተላብሰሽ !

ድንገት ኢትዮ ነኝ ስትይኝ ደነገጥሁ !
ልቤ እገጭ ድው ሲል ተርበተበትሁ !
በኋላም ቀልቤ ተመልሶልኝ ተረጋጋሁ !
በእጅጉ አስገርሞኛል የአጥፊ ኃይላት ጥቃታቸው
አንቺን የረሃብ-ኀማም ተምሳሊት ማድረጋቸው !
ልጆችሽን እርስ-በርስ የሚያናክሱት
ሀብተ-ቅርስሽን የሚዘርፉት !
ነቢዩ አሞጽ ምርጥነትሽን በገለጸው
ለካስ በታላቁ ክብርሽ ቀንተው ነው !!
አንቺማ ምን በድለሻቸው ?

አንቺ እማማ ኢትዮ የንጋት ጸሐይ ጮራ
አሁንም ክብርሽ በዓለም ላይ ደጋግሞ ሲያበራ
ዕቡያን ጠላቶችሽ የደም ዕዳ ያለባቸው
በትንሳኤሽ ያፍራሉ በጣም ቅርብ ነው ጊዜያቸው
የቴሌግራፍ ቴሌግራም ሥራ በዓለም እጅግ ጎልቶ
ብዙ ባለሙያዎችን አፍርቶ
ሕዝብን ከሕዝብ ሀገርን ከሀገር አገናኝቶ
ግንኮ አንቺ ኢትዮ አንቺ እማማ
ድንቅ ስምሽ በኮዱ ውስጥ ተደብቆ ሳይታይ ሳይሰማ !
ከመቶ ሰባ ዓመታት በላይ በቋቱ የተደበቀ ስምሽን
የቀዳሚነትና የታላቅነት አርማሽን !
ፈልፍዬ አወጣሁት እኔው አበሻው ልጅሽ !
የኮዱ ግኝት አጋር ነውና ለሚሊዮን ዓመታት ጥንታዊነትሽ
ኢትዮ እማማ ደስ ይበልሽ !!
እነዚያ ጠላቶችሽ መሠሪዎቹማ
ይኸን ምሥጢር ቀድሞ አውቀውት ቢሆንማ !
አሁን ሊደብቁሽ እንደሚከውኑት ታላቅ ሤራ
ምሥጢሩን ባጠፉት ነበር ድንቅ ስምሽ እንዳይጠራ
እንግዲህ ሮቦቱስ ምን ያውራ ?!!
የኢትዮ ልጅ ሃበሻውም ደስ ይበልህ
ማንነትህ ይበልጥ ተረጋገጠልህ !
ይልቅ ያለፍህበትን ጭለማ አስተሳሰብ ትተህ
በድንቂቱ ኢትዮ ቀዳማዊ ክብሯ ተመክተህ !
ከዘመኑ የዓለም ሥልጣኔ ጋር ተጎዳኝ
ስንፍናን አስወግድ ጎሣ-ጎጥን አታመኻኝ !

ሰውን በሰውነቱ ተቀበለው ፡ በሰውነትህ ይቀበሉህ !
ወገንህን አታግለው በዘርና ቀለም ሥሌትህ
የበቀል በቀል ብቀላ
የአስተሳሰብ አተላ
ቢወራረስ ለትውልድ ሁላ
ምግብ አይደል አይበላ
ሸማ አይደል አይለበስ
እንዲያው በከንቱ መጨራረስ !!
ኋላ-ቀሮች እየተባልን ለሥልጡኖች መሰሳለቂያ
ሀገር-ሕዝብ እንዲጠፉ ሆነን የበቀል በቀል መሸመቂያ
በሃሳብ ሳንጣጣም እየተኳዘን ለየብቻ !
እስከመቼ እንሆናለን የመሠሪዎች መጫወቻ ?
ሀገራችን የዋይታ አምባ !
ሕዝባችን የችጋር ኀማም ሰለባ 1
ይኼኮ አልነበረም ኩራታችን
የቀዳሚነት ግባችን
እስቲ ቆም ብለን እናስብ ሁላችን
የሰው ልጅ ሰው መሆኑ ታውቆ ሰው ተብሎ ሲጠራ
ታዲያ ምንድነው ፋይዳው ዘርና ጎጥ ቆጠራ ?
እኔ ሌላ ምንም አልልህ ወገን ተሳስተሃል ተመለስ
የአንድነቱ ትግልህ ይጠንክር ክብር ኩራትህ ይታደስ
የኢትዮ ልጅ ነኝ ብለህ ኩራ
ለጎሣ ጎጥ አታቅራራ
ይኸው ዛሬ እንዳየኸው ፤ ከሆነም ተረድተኸው
ጎሣ-ጎጥ ኪሣራ እንጂ ቤሳ-ቤስቲን ትርፍ የለው !

በፈጣሪው ዘንድ ታላቅ ክብር የተቸራትን
እባካችሁ አናቃላት የተከበረች እናትን
ወገኖችም ራሳችሁን አታጋልጡ ለውርደት
ለኩሩው ሕዝብነታችሁ ቁሙለት እንጂ በአንድነት !
ሉሲ በሞርስ ኮድ ፍቺ ኢትዮን አስከትላ
ድብቁ ምሥጢር ተገለጸ እንዲያውቀው ዓለም ሁላ
የሞርሱ ኮድ የኢትዮን ገናና ክብር አረጋገጠ
የማንንም ሀገር ሳይጠራ ኢትዮን ብቻ መረጠ !!
ይኸውላችሁ ተፍረጥርጦ የወጣው ምሥጢረ-ኮዱ
አስተውላችሁ ብታነቡና ብትረዱ !

ምሥጢሩን እንዴት አገኘኸው ለሚሉኝ ጥበበኞች
የሞርሱ ዕውቀት ያላቸው ሞያተኞች
ይምጡና ይጠይቁኝ እኔም ልመልስላቸው
ጥበቡ እኔም ዘንድ መኖሩ ቢገባቸው
ፈቃደኛም ከሆኑ ላስተምራቸው
በሞርሱ ስፒድም ከኛ በላይ የለም ብለው የሚቦርቁ
እኔም ፈጣኑ የኢትዮ ልጅ መሆኔን ይወቁ
ሜዳውም ፈረሱም ይኸው በሚል መድረክ ላይ
እንገናኝና ማንነታችን ይታይ
ዕውቀት ጥበብ በሀገር ዳር ድንበር አይገደብ
ላጭር-ረጅም ለወፍራም ቀጭን ሰው አይመደብ
ነጭ ጥቁር ተብሎ በዘርና ቀለም አይለካ
በረጣሪ ቸርነትና በጥረት እንጂ የሚሳካ
ለማንኛውም ለወገኖቼ ያለኝ መልዕክት ይኸውና
1- 3- 5ኛውን መስመር ቁልቁል አንብቡትና
እማማ ኢትዮን አስተውሏት በጥሞና
ከኢትዮ በኋላ ሁለት ፊደል ቢቀረን
እሱም SM ነው እኛን የሚወክለን
SM ሴመቲክ ነው ብለን ብንቀበለው
ኢትዮም ኢትዮ ናት ቋንቋችን ሴመቲክ ነው

E - I - M- H- S- T- O-
T - O - E- I- M- H S-
H - E - T- O- E- I- M-
I - M - H- E- T- O- E-
O - E - I- M- H- E- T-
S - T- O- E- I- M- H-
M - H- S- T- O- E- I -

የኮዱ ፍቺ ኤሽያን አውሮፓን አሜሪካንን አላለም
የአፍሪካ ሀገሮችን የዓረቡን ዓለም ወዘተ....አልጠቀሰም
ኢትዮይዝም ኢትዮስ ኢትዮ ተብሎ የሷ ስም ብቻ ሲነገር
ዓለም ጉድ ይበል ዛሬ ፈጣሪያችንም ይከበር !
እኛና ጠላቶቻችን ጎስቋላ ያደረግናት !
ከዓለም ሀገራት ሁሉ ኢትዮ ግን ምርጥ ናት !
የጉሥቁልናዋ ጊዜ ያልፋል ሃበሻው ተጠራራ
ተነስ በጠላትህ ላይ በኢትዮ አንድነት ኩራ
መጥፎ እሳቤህን ትተህ ታገል ለኢትዮ ትንሳኤ ተስፋ
ያንተም ሕይወት እንዲፋፋ !

የምሥጢራዊው ኮድ ግኝትና የግጥሙ ደራሲ
አበበ አረዳ

2001-2008

በዚህ ታላቅ ግኝት ዙሪያ ሊያወያይ ወይም ሊረዳ የሚፈልግ ፕሮፌሽናልስ ወይም
ማንኛውም ድርጅት በሚከተለው ኢሜል አድራሻዬ ሊጋብዘኝ ይችላል ::

gebere 01 @google mail.com